«. . . ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፦ ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።»

ማቴ.፱፥፲፭—፲፮

# ስምዐ ጽድቅ

## ልዩ ዕትም




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ

☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

ምክትል ዋና አዘጋጅ

ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር

ካሣሁን ለምለሙ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና

ጸሐፊ

ገነት ታደሰ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል

newspaper@eotcmk.org



ጥቃት የተፈጸመባቸው ምእመናን በከፊል

# በጋሞ ሀገረ ስብከት ቦንኬ ወረዳ በጬሻ ቅዱስ ሚካኤል እና ቅዱስ ፋኑኤል ምእመናን ላይ ጥቃት ተፈጸመ

ካሳሁን ለምለሙ

በጋሞ ጎፋ ሀገረ ሰብከት በቦንኬ ወረዳ ቤተ ክህነት የጬሻ ሚካኤልና ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአክራሪዎች ጥቃት እንደተፈጸመባቸው የማኅበረ ቅዱሳን ብሮድካስት አገልግሎት ዘገበ፡፡

የደብሩ አገልጋይ ካህናት ለሚዲያው በስልክ በሰጡት መረጃ መሠረት የጥቃቱ መነሻ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያኑ ዓውደ ምህረት ፴ ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ አንዳንድ የፕሮቴስታንት ዕምነት ተከታዮች የለቅሶ ሥነ ስርዓት እናከናውናለን በማለታቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ጥቃት ፈጻሚ የፕሮቴስታንት ዕምነት ተከታዮች አምልኮታቸውንም ሆነ የልቅሶ ሥነ ስርዓታቸውን የሚያከናውኑበት የራሳቸው የሆነ ቦታ ያላቸው መሆኑን አገልጋዮቹ ጠቁመው በኃይል የለቅሶ ሥነ ስርዓት ያከናወኑበት ቦታ “ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለምን ተሰጠ?" በሚል መልካም ያልሆነ ሐሳብ ተነሳስተው በምእመንና ላይ ጥቃቱን እንደፈጸሙ ገልጠዋል፡፡

አክራሪ የፕሮቴስታንት ኃይሎች ሁከት ፈጥረው ቤተ ክርስቲያኑን ለማፍረስ ድንጋይ ሲወረውሩ እንደነበረና በታጠቋቸው ድምጽ አልባ መሳሪያዎች በመታገዝ በአገልጋይ ዲያቆናትና በአካባቢው ምእመናን ላይ ከፍተኛ የሆነ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ማድረሳቸውን ካህናቱ ለሚዲያው አስረድተዋል ፡፡

ካህናቱ አያይዘውም የአካባቢው የመንግሥት ኃላፊዎችና የጸጥታ አካላት በአጥፊዎቹ ላይ የወሰዱት ሕጋዊ ርምጃ ያለመኖሩን ገልጠው አብዛኛዎቹ የመንግሥት አካላት ከጥቃት አድራሽ የፕሮቴስታንት ኃይሎች ጋር በመሰለፋቸው ጉዳት የደረሰባቸው ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ፍትሕ መነፈጋቸውን ተናግረዋል፡፡




ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ (የሀድያ ስልጤ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ) የመሠረት ድንጋይ ባስቀመጡበት ወቅት

# የወራቤ ደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያንን መልሶ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ ተቀመጠ

*ካሳሁን ለምለሙ*

በአክራሪ እስላሞች ጥቃት የተፈጸመበት በሀድያና ስልጤ ሀገረ ሰብከት የሚገኘው የወራቤ ደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያንን መልሶ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ መቀመጡን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ቲቪ) ዘገበ፡፡

የከንባታና ሀድያ፣ የደቡብና የምዕራብ አፍሪካ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ የደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያንን የመልሶ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ሰኔ ፫ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም ማስቀመጣቸውን ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዕለቱ ንግግር ያደረጉት ብፁዕነታቸው የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት መልሰን አስውበን እንሠራቸዋለን ያሉ ሲሆን ነገር ግን "እኛን የሚያስጨንቀን የፈረሰው ፍቅር፣ የፈረሰው ሰላምና አንድነት ነው" ሲሉ አክለዋል፡፡

አሁን በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ስለደረሰው ጉዳት የምናነሳበባ ወቅት ሳይሆን አዲስ ቤተ መቅደስ የምንገነባበትና የጠበበውንም የምናሰፋበት ጊዜ ነው በማለት ምእመናንን ያጽናኑት ብፁዕነታቸው በጉዳዩ ዙሪያ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር መልካም የሆነ ውይይት ማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ በሀድያና ስልጤ ዞን የሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታይ አባቶች እና የስልጤ ዞን የሃይማኖት ተቋማት ሰብሳቢ ሀጂ መሐመድ ከሊል የተገኙ ሲሆን የወንጌላውያን አማኞች ኅብረት ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ተክለ ሰንበት ተክለ ሥላሴም መገኘታቸው ታውቋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት ሀጂ መሐመድ ከሊል እና አቶ ተክለ ሰንበት ተክለ ሥላሴ በቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ማውገዛቸውን ዘገባው አስረድቶ የቀደመውን የእምነት ተቋማት አንድነትና መተሳሰብ መልሶ ማምጣት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡ በደረሰው ጉዳት ማዘናቸውን ገልጠው የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ ለመገንባት ጥረት እንደሚያደርጉም ቃል ገብተዋል፡፡

የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሕይወት ቀሲስ ንጉሤ ባወቀ በበኩላቸው በመከራ ጊዜ በሃይማኖት መጽናት አስፈላጊ መሆኑን አስረድተው ብፁዕነታቸውን ጨምሮ የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያናችን አካላት ጉዳት የደረሰባቸውን ምእመናን እንዲያጽኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

አካባቢያቸውን ትተው የተሰደዱና ሀብት ንብረታቸው የወደመባቸው ምእመናን አስቸኳይ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱና እንዲቋቋሙ ተከታታይነት ያለው ሥራ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት በኩል እንዲሠራ ሥራ አስኪያጁ አያይዘው አሳስበዋል፡፡

### በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የሚያካሂደውን የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ከግንቦት ፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም. ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ እንዲሁም አገራዊ ሰላምን በማስመልከት ሲወያይ ሰንብቶ ግንቦት ፳፭ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚበጁ የተለያዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ጉባኤውን በጸሎት መዝጋቱ ይታወሳል። በመሆኑም የምልዓተ ጉባኤው ሙሉ መግለጫም እንደሚከተለው ቀርቧል።*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በዓመት ሁለት ጊዜያት እንዲሆን በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ ቁጥር ፻፷፬ በተደነገገው መሠረት ምልዓተ ጉባኤው የመክፈቻው ሥርዓተ ጸሎት ከተፈጸመበት ግንቦት ፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም. ጀምሮ የተለመደውን ዓመታዊ መደበኛ ስብሰባ ሲያካሂድ ሰንብቶ ለቤተ ክርስቲያናችንና ለሀገራችን የሚበጁ ማህበራዊና መንፈሳዊ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡

በዚሁ መሠረት፡-

የ፳፻፲፬ ዓ.ም. የግንቦቱ ርክበ ካህናት ጉባኤ መክፈቻ ንግግር በቤተ ክርስቲያናችንና በአገራችን የተከሰተውን የሰላም እጦት ተከትሎ በደረሰው የሰው ሕይወት ሕልፈትና የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል የካህናትና የምእመናን ሕልፈተ ሕይወት ላይ ያተኮረ ሲሆን በዚሁ ላይ ምልዓተ ጉባኤው በሰፊው ተነጋግሮ ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የተከናወነውን የመንፈቅ ሪፖርት፣ ያዳመጠና የገመገመ ሲሆን በስድስት ወራት ውስጥ ተወስነው ፍጻሜ ያላገኙ ጉዳዮች አስፈላጊው ክትትል እየተደረገ ፍጻሜ እንዲያገኙ ጉባኤው መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ሀገራዊ ሰላምን አስመልክቶም፣ በችግሩ ዙሪያ የተነጋገረው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በአሁኑ ደረጃ በአገራችን ያለው የሰላም እጦት ላይ በሰፊው ተወያይቶ በቀጣይ ጦርነትና የእርስ በርስ ግጭት ተወግዶ አጠቃላይ ሰላም በሚሰፍንበት መልኩ ተነጋግሮ ችግሩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት እንዲቻል፣ ቤተ ክርስቲያናችን የአስታራቂነት ሚናዋን መጫወት እንድትችል ለማድረግ ለፌዴራል መንግሥት ጥያቄ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአገራችን በተከሰተው የሰላም እጦት ምክንያት በቤተ ክርስቲያናችንና በካህናት አገልጋዮቻችን እንዲሁም በምእመናኖቻችን ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው የሰው ሕይወት መጥፋትና የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል፣ የበዓል ማክበሪያ ቦታዎች መነጠቅ አስመልክቶም ጉባኤው የተነጋገረ ሲሆን አጥፊዎች ለሕግ እንዲቀርቡ፣ በቀጣይም በመንግሥት በኩል አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግልን በመጠየቅ፣ እስከአሁን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ደረሰ የተባለው ችግር በዓይነትና በቁጥር ተለይቶ ለሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በአገራችን በተከሰተው ወቅታዊ ችግር ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው፣ ለተፈናቀሉና ለተሰደዱ ወገኖች፣ ለፈረሱና ለተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት ማቋቋሚያ፣ ለተዳከሙ የአብነት ት/ቤቶች መደጎሚያ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግ ተወስኗል፡፡ በትግራይ ክልል የሚገኙ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያኒቱን አስመልክተው በ፴/፬/፳፻፲፬ ዓ.ም እና በ፫/፮/፳፻፲፬ ዓ.ም. ባወጡት መግለጫ ምልዓተ ጉባኤው ገምግሞ በቀጣይ

የክልሉ አባቶች በማዕከል እንደ ቅዱስ ሲኖዶስ አባልነታቸው ለአገር አንድነትና ሰላም በጋራ እንዲሠሩ ምልዓተ ጉባኤው ጥሪውን አቅርቧል፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን በዘመናት በርካታ የልማት ተግባራትን ስታከናውን የቆየች ቢሆንም ለቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት የሚሰጥ የሕክምና ማዕከል ሳታቋቁም መቅረቷ ተገቢ አለመሆኑን በመገምገም፣ በቀጣይ የሕክምና ማዕከሉ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲገነባ ጉባኤው ወስኗል፡፡ በየሦስት ዓመቱ የሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ እና የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ አስመልክቶ በተደረገው ምርጫም፡-

1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የሰሜን አሜሪካ ኒውዮርክና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ (ዶ/ር) የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፣
2. ብፁዕ አቡነ አብርሃም የባሕር ዳር ከተማ ልዩ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ አድርጐ በመምረጥ ለቀጣይ ሦስት ዓመታት እንዲሠሩ ሰይሟል፡፡

በአጠቃላይ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በጉባኤ ላይ በቆየባቸው ቀናት ባደረገው ሰፊ ውይይት፡-

ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት መጠናከር፣

ለአገራችን፣ ለሕዝባችንና ለመላው ዓለም ሰላም መገኘት፣

ለተሰደዱና ከቀያቸው ለተፈናቀሉ መረጋጋትና ወደቀያቸው መመለስ፣

በአገራችን ጦርነትና የሰላም እጦት በሚወገድበት ሁኔታ በሰፊው በመምከርና ለዘለቄታዊ ሰላም አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በርካታ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡

በመሆኑም መላው ሕዝባችንና የመንግሥት መሪዎች ሁሉም ለአገራችን ሰላምና አንድነት ከምንጊዜውም በላይ በአንድነት በመነሣት በትኩረት እንዲሠሩ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ጥሪውን አቅርቧል፡፡

በመጨረሻም የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ከግንቦት ፱-፳፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊና ማህበራዊ እንዲሁም አገራዊ ሰላምን አስመልክቶ ሲወያይ በመቆየት በዛሬው ዕለት ስብሰባውን በጸሎት ዘግቷል፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ለአገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን እንዲሁም ለመላው ሕዝባችን ሰላሙንና አንድነቱን ይስጥልን፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን፡፡

አባ ማትያስ ቀዳማዊ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም

ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ግንቦት ፳፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም.

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

# የማኅበረ ቅዱሳን የ፴ ዓመታት የአገልግሎት የትሩፋት!!!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለሀገራችን ሥልጣኔ በር ከፋች ሆና የኖረች ከመሆኗም በላይ ዛሬ ላለው ዘመናዊ ሥልጣኔም መሠረት የጣለች ባለውለታ ናት። ቀደምት የቤተክርስቲያን አበው ደከመን፣ ሰለቸን ሳይሉ ዐረፍተ ዘመን እስከገታቸው ድረስ ሲያገለግሉ ኖረው ቤተክርስቲያኒቱ አሁን ከምትገኝበት የዕድገት ደረጃ አድርሰዋታል።

በመሆኑም ይህንን አባቶች ወዛቸውን አንጠፍጥፈው፣ ዐይናቸውን አፍዘው፣ ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው በሰማዕትነትና በተጋድሎ ያቆዩትን ሃይማኖት ለማስጠበቅና ለቀጣዩም ትውልድ በተመቻቸ ሁኔታ ለማስተላለፍ በእግዚአብሔር ፈቃድ በቅዱስ ሲኖዶስ ሙሉ ድጋፍና ዕውቅና የተመሠረተው ማኅበረ ቅዱሳን በውጪ በአፅራረ ቤተክርስቲያንና በአሕዛብ፣ በውስጥ ዓላማውን ባልተረዱ፣ ዓላማውን ተረድተው የኑፋቄ ትምህርታቸውን እንደልብ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ለማስረግ ሌት ተቀን በሚተጉ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እየተከሰሰ እየተወቀሰና ያለ ስሙ ስም እየተሰጠው በተጋድሎና በስኬት ፴ ዓመታትን ዘልቋል።

እነዚህ በውስጥና በውጭ የሚገኙት የቤተክርስቲያን ጠላቶች ላለፉት ፴ ዓመታት ቤተክርስቲያን ላይ በየዘመኑ በሚነሳው ፈተና እየተጠቀሙና በምክንያት እየተሳቡ ለቤተክርስቲያን ወዳጅ መስለው እየቀረቡና እያስቀረቡ ማኅበረ ቅዱሳንን ቢቻላቸው እንዲፈርስ፣ ባይቻላቸው ደግሞ የቤተክርስቲያኒቱን ሥርዓት ለማፍረስ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ የሚያስታጥቋቸው መናፍቃን ሴራና ዓላማ እንዳይጋለጥ እና በቤተክርስቲያኒቱ ላይ እንደፈለጋቸው እንዲሆኑ ማኅበሩ አገልግሎቱ ተገድቦ እንዲዋቀር ለማስደረግና ለማድረግ የጥፋት ዘመቻዎችን ሲከፍቱ ዘልቀዋል። ይሁን እንጂ ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን በነዚህ የተጋድሎ ዓመታት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰጠችውን ኃላፊነት ከዳር ለማድረስ ላለፉት ፴ ዓመታት ስኬታማ ሥራዎችን አከናውኗል። በዚህ ዘገባ ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን በሐዋሪያዊ አገልግሎት ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት፣ ግቢ ጉባኤያትን በማቋቋም እና የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ያበረከታቸውን አስተዋጽኦና ስኬቶች በተከታታይ እትሞች በዝርዝር እናሳያለን። ሥራዎቹን በዝርዝር ከማየታችን በፊት ማኅበረ ቅዱሳን ማን ነው? እንዴትስ ተመሠረተ? የማኅበሩ ስያሜውስ ከምን መጣ? የሚለውን እናያለን። ለዘገባው ምንጭ እንዲሆነን ማኅበረ ቅዱሳን ላለፉት ' ዓመታት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያበረከታቸው አስተዋጽኦና ስኬቶቻችንን በመጽሐፍት ለማዘጋጀት የተሰበሰበውን መረጃ በምንጭነት መጠቀማችንን እናሳውቃለን።

## ማኅበረ ቅዱሳን ማን ነው? እንዴትስ ተመሠረተ?

ማኅበረ ቅዱሳን ማን ነው? እንዴትስ ተመሠረተ የሚለውን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት አፅራረ ቤተክርስቲያንና ዓላማቸውን ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱት ተላላኪዎቻቸው የውስጥ ዐርበኞች ማኅበረ ቅዱሳንን በሰው ውስጥ የጥላቻ መንፈስ እንዲያድር ከሚጣጣሩበት መንገድ አንዱ ማኅበሩ የሚጠራበትን ስያሜውን በማዛባት ነው የሚጀምሩት። ከዚህ አንጻር ማኅበረ ቅዱሳን ሲባል ምን ማለት ነው? የሚለውን ነገር ማብራራት ያስፈልጋል። ስለዚህ ስያሜው ላይ አጭር ትንታኔ በመስጠት ወደ ማንነቱና አመሠራረቱ እንለፍ።

## የማኅበሩ ስያሜ

አንዳንድ ሰዎች ስያሜውም ግራ ያጋባቸዋል። ከላይ እንደጠቀስነው አባላቱ ለራሳቸው ያወጡት አስመስለው የሚነግሯቸው ሰዎች አሉና የዋሀኑ ግራ ቢጋቡ አያስደንቅም። ነገር ግን የማኅበሩ ስያሜ እኩያኑ ማኅበሩን ለማጥላላት ከሚጠቀሙት የሀሰት ትርክት በእጅጉ የተለየ ነው። ማኅበረ ሚካኤል «የሚካኤሎች ስብስብ»፣ ማኅበረ ማርያምም «የማርያሞች ስብስብ» ካልሆነ /እንዳልሆነ/ ማኅበረ ቅዱሳንም «የቅዱሳን ሰብስብ» አይደለም። ሊሆን አይችልም፤ ወይም ማኅበረ ጊዮርጊስን የመሠረቱ ሰዎች ራሳቸውን «ጊዮርጊሶች»ነን እንደማይሉት፤ እንዳልሆኑትም፣ ማኅበረ ቅዱሳንም ቅዱሳን ነን የሚሉ ሰዎች ስብስብ አይደለም። ይልቁንም ማኅበረ ማካኤል የሊቀ መላእክት የቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት፣ ተራዳኢነት የሚታሰብበት ማኅበር እንደሆነው ሁሉ ማኅበረ ቅዱሳንም የቤተክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዐት ከመጠበቅና ከማስተማር በተጨማሪ

በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርተ ሃይማኖት መሠረት የቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት እንዲሁም የቅዱሳን መላእክት ክብራቸው፤ ገድላቸውና ትሩፋታቸው፣ አማላጅነታቸውና በረከታቸው፤ በሰፊው እንዲታወቅና ትውልዱም የዚህ ተጠቃሚ እንዲሆን ትምህርት የሚሰጡበት ማኅበር ነው፡፡ ምእመናን በነዚህ ቅዱሳን አማላጅነትና ረድኤት እየታገዙ ለመንግሥተ ሰማያት እንዲበቁ ማድረግም ቀዳሚ ተግባሩ ነው፡፡

ከዚህ የተነሣ የእነዚያ ብዙ ማኅበራት ኅብረት የሆነው ማኅበር የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ ጻድቃን ሰማዕታትና የቅዱሳን መላእክት ሁሉ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ማኅበረ ቅዱሳን ተባለ፡፡

## ማኅበረ ቅዱሳን እንዴት ተመሠረተ?

ዘመኑ የኮምዩኒዝም ርዕዮተ ዓለምና አስተሳሰብ የሰፈነበት፤ ስመ እግዚአብሔርን መጥራት አስቸጋሪ የሆነበትና ወደ ቤተ እግዚአብሔር መሔድ እንደ ኋላቀርነት የሚቆጠርበት ዘመን ነበር ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በተለይም በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ/ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች/ በሚገኙ ተማሪዎች ዘንድ ቃለ እግዚአብሔርን በግልጽ መነጋገርም ሆነ መስማት የማይታሰብበት ወቅት ነበር፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለይም በንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች እንዲያስተምሩ ከምዕራባውያኑ ሀገሮች መጥተው የነበሩ ሚሲዮናውያን የኑፋቄ ትምህርታቸውን ያሠራጩ የነበረውም በእነዚሁ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ ትውልዱ በየአቅጣጫው በሚሲዮናውያኑ የኑፋቄ ትምህርት እንዲሁም በኮምዩኒዝም ርዕተ ዓለምና አስተሳሰብ እየተነጠቀ ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነት የኮበለለበት ከቤተክርስቲያን የራቀበት ዘመን ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ዋናው ግቢ ከፍተኛ ትምህርታቸውን ይከታተሉ የነበሩ አምስት ወጣቶች ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ በቅዱስ ገብርኤል ስም ተሰባስበው ጽዋ መጠጣት የጀመሩት፡፡ ይህ መንፈሳዊ እንቅስቀሴ በዚሁ ተወስኖ አልቀረም፡፡ በየሳምንቱ እሑድ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን ግቢ በመጠለያ ሥር እየተሰባሰቡ በተደራጀ መልክ ባይሆንም መንፈሳዊ ትምህርት ይማሩ ጀመር፡፡ ከዚያም በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት አዳራሽ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ትምህርት መማር ቀጠሉ፡፡

እንዲህ የተጀመረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚገኙ የቤተክርስቲያን ልጆች ዘንድ የተዳረሰበት አጋጣሚና ሁኔታ የተፈጠረው ደግሞ በዚሁ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ነው፡፡ በወቅቱ በነበረው የመንግሥት ሠፈራ ፕሮግራም በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በሙሉ በመንደር ምሥረታና መልሶ ማቋቋም ዘመቻ ወደ ጋምቤላ፣ መተከል እና ፓዌ እንዲዘምቱ ተደረገ፡፡ በዘመቻው ወቅት ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየመጡ የተገናኙት የቤተክርስቲያን ልጆች ቃለ እግዚአብሔርን በመማር፣ በማኅበር ጸሎት በማድረግ እና ስለቤተክርስቲያን ጉዳይ በመወያየት ጊዜውን ተጠቀሙበት፡፡

በዚህ ዓይነት የተጀመረው እንቅስቃሴ ከዘመቻው መልስ በ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ተጠናከረ፡፡ ውስን የነበረው የተማሪዎች ቁጥርም ጨመረ፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ አራት ኪሎ ግቢዎች እስከ አርባ የሚደርሱ ተማሪዎች በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ማኅበር አዳራሽ እየተገኙ ትምህርተ ወንጌል ይማሩ ነበር፡፡ የተማሪዎቹን ዓላማና ጥረት የተገነዘቡ አባቶች መምህራነ ወንጌልም በቅርብ ሆነው እየተከታተሉ ሲያስተምሯቸው ቆይተዋል፡፡

በቀጣዩ ዓመት ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፸ ዓ.ም ድረስ ተማሪዎቹ በተምሮ ማስተማር ማኅበር አደራሽ ከሚከታተሉት መንፈሳዊ ትምህርት መርሐ ግብር ጋር ይህ መንፈሳዊ እን ቅስቃሴ ተጠናክሮ በስፋት የሚቀጥልበትን መንገድ ይወያዩ ነበር፡፡ በወቅቱ ትኩረት ተሰጥቶት ውይይት ይደረግበት የነበረው ዐቢይ ጉዳይ ከመካከላቸው ሰባኪ ወንጌል ማፍራት ነበር፡፡ ለዚህም በተለይ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመግባታቸው በፊት በቤተክርስቲያን አገልግሎት እየተሳተፉ በሰንበት ትምህርት ቤት ያደጉና በመጠኑም ቢሆን ልምድ ያላቸውን ተማሪዎች እንዲያስተምሩ ማድረግ አንድ መፍትሔ ነበር፡፡ ለዘለቄታው ግን ከተማሪዎቹ መካከል በወቅቱ ሸዋ ሀገረ ስብከት ዝዋይ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የካህናት ማሠልጠኛ ገብተው እንዲሠለጥኑ ማድረግ የታመነበት መሠረታዊ ጉዳይ ሆነ፡፡

ይህንኑ ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ፤ አስቀድመው በዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ ገብተው ስለስብከተ ወንጌል ሥልጠና የወሰዱ፤ በወቅቱ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ የዝዋይ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም እና የካህናት ማሠልጠኛው የበላይ ጠባቂ ከነበሩትና ለማኅበሩ መመሥረት ትልቅ አስተዋጽኦ ከነበራቸው ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ጋር ይቀራረቡ በነበሩ ተማሪዎች አማካኝነት ግንኙነት ተደረገ፡፡

እንዲሁም በ፲፱፻፸ ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ ግቢ ትምህርታቸውን ሊከታተሉ ከገቡት መካከል እስከ ኀምሣ የሚደርሱ ተማሪዎች በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት ተሰብስበው ይማሩ ጀመር፡፡ በዚሁ ዓመት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚማሩ ተማሪዎችም ተመሳሳይ መንፈሳዊ መርሐ ግብር ጀምረው ነበር፡፡

በዩኒቨርሲቲ መደበኛ ትምህርታቸውን አጠናቀው በ፲፱፻፸ ዓ.ም ከተመረቁት ተማሪዎች ውስጥ በግቢ ቆይታቸው በቤተክርስቲያን ተሰባስበው መንፈሳዊ ትምህርት ሲማሩ የነበሩት የቤተክርስቲያን ልጆችም ለመጀመሪያ ጊዜ ተመረቁ፡፡ የምረቃው መርሐ ግብር የተካኼደው በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ማኅበር አዳራሽ ነው፡፡ በበዓሉ ላይ ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮሰ ካልዕ ጋር ሌሎችም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተገኝተው፤ ተመራቂዎቹ ተማሪዎች ለቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲተጉ አስተምረው ባርከው መርቀዋል፡፡

ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ጋር በተደረገው ግንኙነት መሠረት በዚሁ ዓመት ከተመረቁት መካከል ዐሥራ ሁለት ተመራቂ የቤተክርስቲያን ልጆች በዝዋይ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ካህናት ማሠልጠኛ ገብተው በክረምቱ ወራት፤ ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነት፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ ትውፊት እንዲሁም ሥነ ስብከት ሲማሩ ከረሙ፡፡ ሥልጠናውን የተከታተሉት ተማሪዎች ተመርቀው ከገዳሙ ሲሔዱ፤ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮሰ ካልዕ፤ «ከዚህ ስትወጡ ተበትናችሁ እንዳትቀሩ አደራ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችሁ እየተገናኛችሁ መወያያ ይሆናችሁ ዘንድ መሰባሰቢያ አብጁ» በማለት፤ ተመራቂዎቹ በጽዋ ማኅበር ስም በመሰባሰብ፣ በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ ስብከተ ወንጌልን እንዲያስፋፉ፣ በየዓመቱም በዝዋይ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም እየተገናኙ ስለ ዓመቱ የአገልግሎት ቆይታቸው ሪፖርት እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ አሳስበው አሰናበቷቸው፡፡

ተመራቂዎቹ የቤተክርስቲያን ልጆች የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕን አባታዊ ምክርና መመሪያ አልዘነጉም፡፡ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ «ማኅበረ ማርያም» በሚል ስያሜ የጽዋ ማኅበር መሠረቱ፡፡ በአዲስ አበባና በዙሪያው በሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በዓውደ ምሕረትና ሌሎች መርሐ ግብሮች ቃለ እግዚአብሔርን እያስተማሩ በየወሩ እየተገናኙ ስለአገልግሎታቸው ይወያዩ ነበር፡፡ በዓመቱ መጨረሻም በዝዋይ ተገኝተው ሪፖርት አድርገዋል፡፡ በ፲፱፻፸፩ ዓ.ም ክረምት ለሁለተኛ ዙር ሥልጠና በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔዓለም ተምሮ ማስተማር ማኅበር እና በግቢ ገብርኤል ዓምደ ሃይማኖት አዳራሾች ይማሩ ከነበሩት መካከል ዐሥራ ሁለት ተማሪዎች ተወክለው በዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ አማካኝነት ሥልጠና ተሰጧቸዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች መንፈ ሳዊ እንቅስቃሴው እየተጠናከረ ቀጥሎ በተለይም በ፲፱፻፸፪ ዓ.ም በብዙ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተዳረሰ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ፋኩልቲዎች፤ በጥቁር አንበሳ ሕክምና ፋኩልቲ፣ በልደታ ሕንፃ ኮሌጅ፣ በደብረ ዘይት እንስሳት ሕክምና ፋኩልቲ እንዲሁም በጅማ ጤና ሳይንስ፣ በዓለማያ ዩኒቨርሲቲ፣ በወቅቱ በአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ወዘተ ተስፋፋ፡፡ በዓመቱ የክረምት ወራት ከየዩኒቨርሲቲ እና ኮሌጆቹ የተውጣጡ ፵፰ ተማሪዎች ዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ ገብተው ሥልጠና ወስደዋል፡፡ በሥልጠናው በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ከሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ አርባ የሚደርሱ ተማሪዎችም ተሳትፈዋል፡፡ በዚያ ሥልጠና ወቅት ነበር ባልታሰበ ሁኔታ የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በመኪና አደጋ ማረፋቸው በድንገት የተሰማውና በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ታላቅ ኀዘን የደረሰው፡፡

በወቅቱ ማለትም በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም በነበረው መንግሥት በሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች በሙሉ ወታደራዊ ሥልጠና እንዲወስዱ ሲታዘዝ፤ በሀገሪቱ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጆችና ተቋማት የሚማሩ ፲፩ ሺህ ያህል ተማሪዎች በብላቴ አየር ወለድ ማሠልጠኛ እንዲገቡ ተደረገ፡፡ ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ በዩኒቨርሲቲዎች በኮሌጆች ግቢዎች ተጀምሮ ቀስ በቀስ የተስፋፋው መንፈሳዊ

እንቅስቃሴም የበለጠ የሰፋበትና የተጠናከረበት ጊዜ ሆነ፡፡ ተማሪዎቹ ቀን ከሚሰጣቸው ወታደራዊ ሥልጠና መልስ ማታ ማታ እየተገናኙ መንፈሳዊ ትምህርት መማር በጋራ መጸለይ ጀመሩ፡፡ መንፈሳዊ ትምህርቱና ጸሎቱ በኅብረት የሚካኼደው በወታደራዊ ማሠልጠኛ ካምፑ በሚገኝ በሌላ አገልግሎት ያልተያዘ አዳራሽ /ኬስፖን/ ውስጥ ነበር፡፡ ትምህርቱ ከዚህ ቀደም በዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ ገብተው በሠለጠኑ እና ሌሎችም በቤተክርስቲያን ትምህርትና አገልግሎት በቆዩ ተማሪዎች እየተሰጠ በየቀኑ ምሽት መርሐ ግብሩ ሳይታጎል ለሁለት ወራት ቀጥሏል፡፡ በዚህ ጉባኤ እስከ አምስት መቶ የሚደርሱ ተማሪዎች ያለማቋረጥ ይከታተሉ ነበር፡፡

በወቅቱ በብላቴ አየር ወለድ ማሠልጠኛ ካምፕ ለወታደራዊ ሥልጠና የገቡት ተማሪዎች ማታ ማታ እየተሰበሰቡ በአንድነት ከሚያደርጉት ጸሎት እና ከሚማሩት የቤተክርስቲያን ትምህርት በተጨማሪ፤ በአካባቢው ወደሚገኘው ብላቴ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እየተደበቁም እያስፈቀዱም በመሄድ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን ይሳተፉ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሰባሰቡት ተማሪዎች ኅብረት እየጠነከረ መንፈሳዊ እንቅስቃሴውም እየሰፋ መጣ፡፡ እነዚህ የቤተክርስቲያን ልጆች በወታደራዊ ማሠልጠኛ ካምፕ በነበሩበት ጊዜ የ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የእመቤታችንን የልደት በዓል/ ግንቦት ልደታ/ ለጸሎትና ለመንፈሳዊው ትምህርት በሚሰበሰቡበት አዳራሽ በደመቀ ሁኔታ አከበሩ፡፡

በብላቴ አየር ወለድ ማሠልጠኛ ካምፕ የነበረው የተማሪዎቹ ወታደራዊ ሥልጠና የሁለት ወር ቆይታ በመንግሥት ለውጥ ምክንያት ሊበተን ግድ ሲሆን፤ ተማሪዎቹ በወታደራዊ ካምፑ ቆይታቸው የነበረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ኅብረታቸው ዕጣ ፈንታ አሳሰባቸው፡፡ ይህ መንፈሳዊ አንድነት እንዴት መቀጠል እንዳለበት ተነጋገሩ፡፡ ከብዙ ውይይት በኋላም ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ በየዩኒቨርሲቲና ኮሌጆቻቸው ሲመለሱ በቅዱስ ሚካኤል ስም ተሰባስበው ቤተክርስቲያንን ለማገልገል በመስማማት ቃል ገብተው ተለያዩ፡፡

በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ዕረፍት ዓመታዊ መታሰቢያ ላይ የተገኙ ደቀመዛሙርትና መምህራን ሐምሌ ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም በወቅቱ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ፣ የገዳሙና የካህናት ማሠልጠኛው የበላይ ጠባቂ በነበሩበት በብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገብርኤል ሰብሳቢነት ጉባኤ ተደርጎ ነበር፡፡ በጉባኤው ላይ «በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ተምራችሁ በማኅበረ ማርያም የታቀፋችሁ፣ በየቦታው ያላችሁ፣ በገዳሙም የምትኖሩ መነኮሳት እንዳትበታተኑ በአባታችን ስም ማኅበር አቋቁሙ» በማለት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሐሳብ አቀረቡ፡፡ በሐሳቡ ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ ለጊዜው «የዝዋይ ደቀመዛሙርትና መምህራን ማኅበር» በሚል ስያሜ እንዲጠራ ተወስኖ ማኅበር ተመሠረተ፡፡

ከዚህ ቀደም በ፲፱፻፹፩ ዓ.ም በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም በተምሮ ማስተማር ማኅበር እና በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት የሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ጉባኤ አንድነት በመፍጠር የተጠናከረ እንቅስቃሴ ባያደርግም «ማኅበረ እስጢፋኖስ» የሚባል ማኅበር መሥርተው ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም ቢሆን እንቅስቃሴአቸው የተጠናከረ ባይሆንም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ፋኩልቲ ተማሪዎች «ማኅበረ ሥላሴ» በሚል ስያሜ፤ በሌሎችም ፋኩልቲዎችና ኮሌጆች ግቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በተለያዩ ቅዱሳን ስም በሰየሟቸው ጽዋ ማኅበራት ተሰባስበው ነበር፡፡

በጥር ወር ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት አዳራሽ የመጀመሪያውንም የመጨረሻውንም ጠቅላላ ጉባኤውን ያደረገው «ማኅበረ ሚካኤል» የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ አጽድቆ አመራሩንም መርጧል፡፡ ሆኖም በቅዱሳኑ ስም ማኅበር መሥርተው የተሰባሰቡት አባላት፤ «ዓላማቸው፣ አገልግሎታቸውም ሆነ ታሪካቸው አንድ ነው፡፡ ለምን አንድ ስያሜ ይዘው በአንድነት አይንቀሳቀሱም?» የሚል ሐሳብ በውስጣቸው እየተነሣ በተለያዩ አጋጣሚዎች በጉዳዩ ሲወያዩበት ቆዩ፡፡

በዝዋይ ለተመሠረተው ማኅበር ስያሜ ለመስጠት አዲስ አበባ በብፁዕ አቡነ ገብርኤል ቤት በዚሁ ዓመት በየካቲትና መጋቢት ወራት በተካኼደው ስብሰባ ላይ ሐሳቡ ቀርቦ ውይይት ተደረገበት፡፡ በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ገብርኤል «ሁላችሁም የያዛችሁት አገልግሎት የቅዱሳን ክብር የሚገለጽበት ነው፡፡ ስለዚህ የማኅበራችሁም ስም ‘ማኅበረ ቅዱሳን’ ይባል፡፡» በማለት

ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት፤ የ«ማኅበረ ማርያም»፣ «ማኅበረ ሚካኤል» እና «የዝዋይ ደቀመዛሙርትና መምህራን ማኅበር» ተዋሕደው የሁሉም ማኅበራት የጋራ የሆነው ማኅበረ ቅዱሳን ተመሠረተ።

አባላቱም መንፈሳዊ አገልግሎታቸው የቅድስት ቤተክርስቲያንን ሥርዓትና መዋቅር ጠብቆ በቤተክርስቲያን አስተዳደር ዕውቅና ማግኘት እንዳለበት አምነው፤ «በጠቅላይ ቤትክህነት በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ሆነን እናገልግል» በማለት መተዳደሪያ ደንባቸውን ይዘው ወደ መምሪያው ጽ/ቤት ቀረቡ። በዚህ ዓይነት ማኅበረ ቅዱሳን ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተክርስቲያኒቷ መዋቅር ዕውቅና አግኝቶ ግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በጠቅላይ ቤተክህነት በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር መደራጀቱ ይፋ ሆነ። በዚህ ወቅት ለማኅበሩ ምሥረታ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊዎች ትልቅ አስተዋጽኦ ነበራቸው።

## የማኅበሩ ሚና ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት

### ወንጌልን በቃል

በዘመነ ሥጋዌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርተ ወንጌልን በቃሉ አስተምሮ እንዲሁም ለሐዋርያት ቃሉን በዓለም እንዲዘሩ ‹‹ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ለፍጥረትም ሁሉ ወንጌልን ስበኩ›› ብሎ ባዘዛቸው መሠረት ወንጌል በምንኖርባት ምድር ለዘመናት ስትሰበክ ኖራለች። ቅዱሳን አባቶቻችንም ለእኛ ለሐዲስ ኪዳን ሰዎች ቃሉን በአደራ እንዳስረከቡንም በተመሳሳይ መልኩ ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የእግዚአብሔርን ቃል አስተምረን በሃይማኖትና በክርስቲያናዊ ምግባር ኮትኩተን ማሳደግ ኃላፊነታችን ነው። (ማር.፲፮፥፲፭)

ማኅበረ ቅዱሳን የስብከተ ወንጌልን አገልግሎት በማስፋፋት እና በማጠናከር ረገድ በተለያዩ ጊዜያት በየሀገረ ስብከቱ በተመረጡ ወረዳዎችና አጥቢያዎች እንዲሁም ርእሰ ጉዳዮች ጉባኤያትን በመዘርጋት ትምህርተ ወንጌል ሲያስፋፋ ቆይቷል። የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ደግሞ ምእመናንና አገልጋዮች እንዲጸኑና እንዲበረቱ እንዲሁም ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የወጡትን ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ አድርጓል። በተለይም ከዋናው ማእከል በሚደረገው ድጎማ በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች እና ቋንቋንዎች አገልጋዮችን በድጎማ በመቅጠር አገልግሎቱ በንግሥ በዓል፣ በሠርግ ሥነ ሥርዓት፣ በለቅሶ እንዲሁም የቤት ለቤት አገልግሎት ጭምር በመስጠት ምእመናን የሥላሴን ልጅነት እንዲያገኙ አድርጓል።

በተጨማሪም ከዋናው ማእከልና ከበጎ አድራጊ ምእመናን ጋር በመተባበር በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ የሚያገለግሉ ሰባክያንን እንዲሁም መምህራንና ካህናትን በማሠልጠን የስብከተ ወንጌልን ተደራሽነት ማስፋፋት ችሏል። ሥልጠናዎቹ ሲሠጥባቸው የነበሩ ቦታዎችም ጽርሐ ጽዮንና ዝዋይ ካህናትና መምራን ማሠልጠኛ የነበሩ ሲሆን እንደሥልጠናው ሁኔታም ተከናውኖዋል። በእነዚህ የአገልጋዮች ማሠልጠኛ ተቋማት የሠለጠኑ አገልጋዮችም በአገልግሎት ተሠማርተው ይገኛሉ።

በዚህም መሠረት ስብከተ ወንጌል ባልተስፋፋባቸው ወረዳዎች ሐዋርያዊ ጉዞ በማድረግ ወንጌልን ለምእመናን ማድረስ እንዲሁም በዓመት ሁለት ጊዜ የሐዊረ ሕይወት ጉዞ በማድረግ በከተማ እና በገጠር ላሉ ምእመናን ወንጌልን ማስተማር ተችሏል። ማእከላት ባደረጉት የሐዊረ ሕይወት ጉዞ ምእመናን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በሰፊው አግኝተዋል። በተለያየ ጊዜ በሃይማኖት ምክንያት የሚነሡ የተለያዩ ጥያቄዎች በመምህራን መልስ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በተለይም በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች በነበረው መጠነ ሰፊ የተሐድሶ እንቅስቃሴ በማእከላቱ አዘጋጅነት በተሠጠው ሰፊ የጸረ ተሐድሶ ሥልጠናና ጉባኤ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እንቅስቃሴያቸውን ለመግታት የተቻለና ምእመናንም ሰፊ ትምህርት እንዲያገኙ፣ በጉዞ በሄዱባቸው ቤተ ክርስቲያናትም በአገልግሎት እንዲበረቱ የተለያዩ ድጋፎች መደረጋቸውን የሚጠቁመው መረጃው። ለምሳሌ ማኅበረ ቅዱሳን ከባለ ድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር በመቀናጀት ቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት ሳልደረሳቸው ወገኖች በማስተማርና ተደራሽ በማድረግ እስከ አሁን ከ፮፼፲፱፻፸፬ (ስድሳ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት) በላይ አዳዲስ አማንያን አስጠምቋል። እነርሱም የሚያስቀድሱበት፣ የሚጸልዩበትና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሳተፉበት ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት በማስፈለጉ ሰባት ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናትን አስገንብቶ በማስመረቅ ለአዳዲስ አማንያኑ አገልግሎት እንድሰጡ ማድረጉንም ጠቁሟል። አዲስ አማንያንን ለማስጠመቅና በምግባር በሃይማኖት

ለማጽናት የሚያግዙ በርካታ ጉዳይ ተኮር ጉባኤያትን ተከናውኗል።

አዳዲስ አማንያኑም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እስኪገነባላቸው ድረስ የሚሰበሰቡበት፣ እግዚአብሔርን በአንድነት የሚያመሰግኑበትና ቃለ እግዚአብሔርን የሚማሩበት የስብከት ኬላ (መካነ ስብከት) አዳራሽም ተሠርተዋል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን ለማስተማር የሚሰማሩ ሰባክያነ ወንጌልን በተለያዩ ማሰልጠኛ ማእከላት በማሰልጠንም ማሰማራቱን የሚገልጸው መረጃው፤ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን በተለያዩ ቋንቋዎች ተደራሽ የሚያደርጉ ፱፻፬፻፺ (ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ዘጠና) ሰባክያነ ወንጌል በማሠልጠን ማሰማራት ተችሏል።

እንዲሁም በውጪ ሀገር የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎት መሠማራት ለሚችሉ ፭፻፶፰ (አምስት መቶ ኀምሳ ስምንት) አገልጋዮች ሥልጠና ተሰጥቷል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን አገልግጋዮችን በክብረ ክህነት ጥበቃ ለማሰማራት ፶፮፻፹፯ (ለአምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት) አገልጋዮችና መምህረ ንስሐ ካህናትን በስብከተ ወንጌል ለማሰማራት ፵፻፱፻፸፫ (ለአራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሦስት) ካህናት ሥልጠና ተሰጥቷል። የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ትኩረት በሚፈልጉ እና ቅድሚያ በሚሰጣቸው ኩታ ገጠም በሆኑ እያንዳንዳቸው ፮ ወረዳዎችን ታሳቢ ያደረጉ ከ፴፮ በላይ ሐዋርያዊ ጉዞዎች ተከናውነዋል።

አዳዲስ አማንያንን ለማስጠመቅና በምግባር፣ በሃይማኖት፣ ለማጽናትና የጠፉትን ለመመለስ የሚያግዙ ቅድሚያ በሚሰጣቸው አካባቢዎች ከ፲፻፰፻፹፱ (ከአንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ) በላይ ጉዳይ ተኮር ትምህርታዊ ጉባኤያትን ማከናወንም ተችሏል። ምእመናንን በምግባር በሃይማኖት ለማጽናት፣ አዳዲስ አማንያንን ለማስጠመቅና በምግባር በሃይማኖት ለማጽናትና የጠፉትን ለመመለስ ለሚያገለግሉ ፯፻፲ አገልጋዮች ወርኃዊ ደመወዝ እንዲከፈላቸውም ተደርጓል። በእነዚህ አገልጋዮች በተለያዩ አካባቢዎች ፭፻፸፻፮፻ (ኀምሳ ሰባት ሺህ ስድስ መቶ) ጉዳይ ተኮር ጉባኤያት ተከናውነዋል።

አዳዲስ አማንያን የሥላሴን ልጅነት ካገኙ በኋላ የሚያስቀድሱበት፣ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣

**በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ገብርኤል «ሁላችሁም የያዛችሁት አገልግሎት የቅዱሳን ክብር የሚገለጽበት ነው። ስለዚህ የማኅበራችሁም ስም ‘ማኅበረ ቅዱሳን’ ይባል።» በማለት ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት፤ የ«ማኅበረ ማርያም»፣ «ማኅበረ ሚካኤል» እና «የዝዋይ ደቀመዛሙርትና መምህራን ማኅበር» ተዋሕደው የሁሉም ማኅበራት የጋራ የሆነው ማኅበረ ቅዱሳን ተመሠረተ።**

ልጆቻቸውን ክርስትና የሚያስነሡበትና፤ ተሰባስበው መንፈሳዊ ትምህርት የሚያገኙበት አብያተ ክርስቲያናት መገንባት በማስፈለጉ በተለያዩ አካባቢዎች ፴፱ አብያተ ክርስቲያናት ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ አማንያን የሚሰባሰቡበትና የሚማሩበት ፵፫ የስብከት ኬላ (መካነ ስብከት) አዳራሾች ተገንብተዋል። በካህናት እጥረት የተዘጉ ፸፵ አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ተሟልተውላቸው እንድከፈቱና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግም ተችሏል፡፡ ሕፃናትና ወጣቶችን ተተኪ ትውልድ ከማድረግ አንጻር በገጠራማ እና ጠረፋማ አካባቢ የሚገኙ ፰ ሰንበት ት/ቤቶች እንዲመሠረቱና እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡

ከአዳዲስ አማንያን መካከልም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ለማፍራት ፱፻፲፪ የሚሆኑ የአዳዲስ አማንያን ልጆች የአብነት ትምህርት እንዲማሩ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ወገኖች ስብከተ ወንጌልን ተደራሽ ከማድረግ አንፃርም፤ በማረሚያ ቤቶች ላሉ ወገኖች፣ ለዓይነ ሥውራንና ለሌሎችም አካል ጉዳተኞች ተከታታይ ትምህርቶች በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ስብከቶችን፣ መዝሙራትን እና መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችን ጨምሮ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በወላይትኛ፣ በቤንችኛ፣ በአሪኛ፣ በሲዳምኛ፣ ጉራጌኛ፣ ኮንሶኛ፣ ጋሞኛ፣ ጌዲዮኛ፣ ከምባትኛ እና ሌሎች ቋንቋዎች ተዘጋጅተው ከአንድ ሚሊዮን ቅጂ በላይ ለምእመናን ተሠራጭተዋል፡፡

እንዲሁም ተማሪዎችን ብቁ አገልጋይ የማድረግ ተልእኮውን ለማሳካት የትምህርተ ሃይማኖት፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ፣ ሥርዓትና ትውፊት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ለማስተማር በከፈተው የአቡነ ጎርጎርዮስ ትምህርት ቤቶች እያሳካ ይገኛል፡፡

### የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በመገናኛ ብዙኃን (ቲቪ፣ ማኅበራዊ ገጾች)

ማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌል ከሚያስፋፋባቸው መንገዶች ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎቹ የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ ማኅበሩ በእነዚህ ሚዲያዎቹ የሚያስተላልፋቸውን ትምህርተ ሃይማኖት በተደራጀ መልኩ ወደ ምእመናን ለማድረስ ያመች ዘንድ የሚዲያ ዋና ክፍል ያዋቀረ ሲሆን ይህም የቴሌቭዥን አገልግሎት ተቋም ነው፡፡

የቴሌቭዥን ክፍሉም በሥሩ የሬዲዮ ዝግጅት ክፍል፣ በኢቢ. ኤስ ቴሌቪዥን የአየር ሰዓት ይቀርብ የነበረ የቴሌቪዥን ዝግጅት እና የቀጥታ የኢንተርኔት ሥርጭት ቴሌቪዥን ዝግጅት ክፍል ነበር፡፡ ማኅበሩ ክፍሉን ከማቋቋሙ በፊት በሰሜን አሜሪካ ባሉት ሁለት የመካከለኛ ሞገድ የሬዲዮ ጣቢያዎች፣ በአውሮፓ ማእከል በሚካሄድ ፓል ቶክ እና በሰሜን አሜሪካ ማእከል አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ ይሰራጭ በነበረው የአጭር ሞገድ የሬዲዮ ሥርጭት ስብከተ ወንጌልን ሲያስፋፋ ቆይቷል፡፡ ዛሬም ላይ የሬዲዮ መርሐ ግብሩን በኢንተርኔት እያስተላለፈ የሚገኝ ሲሆን በኢቢ.ኤስ የቴሌቪዥን ጣቢያ ይተላለፍ የነበረው መርሐ ግብሩ ቢቋረጥም በ፲፩ (0ሥራ አንድ) የውጭ ሀገራት በኢንተርኔት መረብ አማካኝነት መርሐ ግብሩ የቀደመ ይዘቱን ሳይለቅ ሥርጭቱን ሲያስተላልፍም ነበር፡፡

ከየካቲት ወር ፳፻፯ ዓ.ም ጀምሮ የአገልግሎት አድማሱን ይበልጥ ተደራሽ በማድረግ በቀጥታ የኢንተርኔት ሥርጭት የቴሌቪዥን መርሐ ግብር ያስተላልፍ እንደነበርም የሚታወስ ነው፡፡ በአጠቀላይ ከ፳፻፯-፳፻፱ ዓ.ም. በአማርኛ ሳምንታዊ በኦን ላይን ቲቪ እና ሬዲዮ ላይ ብቻ ተወስኖ የነበረ አገልግሎትን ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም ይህም በወቅቱ ጊዜ ወስዶ ጥራት ያላቸውን መርሐ ግብራት ለመሥራት ጥሩ አጋጣሚ መፍጠር ችሏል፡፡

ለዚህ አገልግሎትም በቂ የሰው ኃይል የነበረ በመሆኑ በመስክ ሥራም በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ እነዚህ ሥራዎችም በአሌፍ ቴሌቪዥን መርሐ ግብሩ ሲጀምር እንደመጠባበቂያ ሥራ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋም በኢ.ቢ.ኤስ ቴሌቪዥን ጣቢያ ይተላለፍ የነበረው ልምድ ቀላል አልነበረም በአጠቃላይ ይህንን ልምድ እንደመነሻ ይዞ በመነሣት ከ፳፻፲ ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አደረጃጀት በአሌፍ የቴሌቪዥን ጣብያ በትግርኛ በኦሮምኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች ስብከተ ወንጌልን በሳምንት ለ፲፬ (0ሥራ አራት) ሰዓት ሲያስተላልፍ መቆየቱንም የሚታወስ ነው፡፡ በአሌፍ ቴሌቪዝን የአየር ሰዓት ኪራይ አጀማመሩ በሰባት ሰዓታት ቢሆንም በያዘው ስልታዊ እቅድ መሠረት

በየዓመቱ ሰዓቶችን በመጨመርና፣ የመርሐ ግብር ይዘት ጥራት ማሻሻያዎችን በማድረግ አገልግሎቱን ወደ ፲፬ ሰዓት ማሳደግ ተችሎም ነበር።

## የ፳፬ ሰዓት የቴሌቭዥን አገልግሎት

ማኅበሩ ይህን ክፍል በተቋም ደረጃ ባቋቋመ በአጭር ጊዜያት ውስጥ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚጠቅሙ በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል። በመሆኑም አገልገሎቱን መጠቀም የሚፈለጉ አካልት ዕለት በዕለት በቁጥር እና በዓይነት በመጨመራቸው በዓለማዊ ሚድያ ላይ ተጨማሪ ሆኖ መንፈሳዊ መርሐ ግብር ማቅረብ ያስከተለው ክፍተት፣ የማኅበሩ የአየር ሰዓትን ለማሳደግ ፍልጎት በመጨመሩ በአሌፍ ቴሌቭዥን ጣቢያ ላይ የነበረውን የአየር ሰዓት ኪራይ ለሁለት ዓመታት ሲጠቀም ቆይቶ ከ፳፻፲፪ ዓ.ም ከመስከረም ወር ጀምሮ ሙሉ በሙሉ የራሱ የሆነ የ፳፬ (ሃያ አራት) ሰዓት መንፈሳዊ የቴሌቭዥን ጣቢያ ሊከፍት ችሏል።

በዚህም ቀድሞ የነበረው አገልግሎት በቂ ባለመሆኑ እና የበለጠ አገልግሎቱን በተለያዩ ቋንቋዎች ተደራሽ ለማድረግ በልዑል እግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ‹‹የማኅበረ ቅዱሳን ቲቪ›› የሚል የሙሉ የ፳፬ ሰዓት አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። የቴሌቪዥን መርሐ ግብሩ ለብዙ ነፍሳትም የመዳን ምክንያት ሆኗል። ስለ ማኅበረ ቅዱሳን ምንነት ያልተረዱ ሰዎችም ማኅበሩን በግልጽ እንዲያውቁ ማድረጉንም አመልክቷል። በማኅበሩ ፴ኛ የምሥረታ በዓል ላይም የቴሌቪዥን መረሐ ግብሩ የቀጥታ ሥርጭት መጀመሩን ማብሠሩም ይታወቃል።

በማኅበሩ የቴሌቪዥን ጣቢያም በአማርኛ፣ በትግርኛ፣ በኦሮምኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ መርሐ ግብራሮች (በመደበኛና ኦን ላይን የሚተላለፉ)፣ የሬዲዮ መርሐ ግብሮች በቪሲዲ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ትምህርቶች እና ስብከቶችን እንዲሁም ፊልሞች መምህራንንና ሌሎች አባላቱን በማስተባበር የስብከተ ወንጌል በአማርኛ፣ በግእዝ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በዓለም ደረጃ እንዲስፋፋ የበኩሉን ጥረት አድርጓል።

## ድረ ገጽ፣ ፌስ ቡክ፣ ቴሌግራም፣ ትዊተር እና ኢንስተግራም

ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ካለው ቁርጠኝነት የተነሣ ማኅበረ ቅዱሳን ከኅትመት መገኛኛ ብዙኃኖች በተጨማሪ ባደራጀው የመዛግብት እና መረጃ ክፍል ሥር በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም የአማርኛ ድረ ገጽን በመዘርጋት አገልግሎቱን ቢጀምርም ብዙም ሳይቆይ ከኦሮምኛና ከእንግሊዘኛው ድረ ገጾች በተጨማሪ ፌስ ቡክ፣ ቴሌግራም፣ ትዊተር እንዲሁም ኢንስታግራም በመክፈት ወንጌልን ለአንባብያን ተደራሽ እያደረገ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ማኅበሩ የሚያሠራጫቸው ትምህርተ ወንጌል የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት የሚጠብቁ፣ ታሪክ የማያፋልሱ፣ የምእመናንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት የሚያሳድጉ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን የሚያስተምሩ እንዲሆኑ ለማድርግ የራሱን የአርትዖት አገልግሎት ማስተባበሪያ አቋቁሞ በከፍተኛ ጥንቃቄ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። አሁንም ሥነ ጽሑፎች (ኪናዊ) እና የሥነ ሥዕል አገልግሎት ሥራዎች በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃኖች ወቅቱን ተከትሎ ለአንባብያን ተደራሽ እንዲሆኑ እያደረገ ነው።

## ወንጌልን በጽሑፍ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በቅዱስ ቃሉ እንዳስተማረን ሁሉ ሐዋርያት የእርሱን ስብከት እና ያደረገውን ተአምራት በሙሉ ለትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር በአምላካችን ቅዱስ ፈቃድና ትእዛዝ በጽሑፍ አስተላልፈውልናል። ከመጽሐፍ ቅዱስም በተጨማሪ አዋልድ መጻሕፍትን ጨምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትንም በአደራ አስረክበውናል። ስለዚህም ይህን አደራ ለመወጣት ማኅበረ ቅዱሳን ዓላማዬ ብሎ ከሚተገብራቸው መንፈሳዊ ተግባራት መካከል የስብከተ ወንጌልን ተደራሽ አድርጓል።

## ሐመር መጽሔት

የዐውደ ምሕረት ጉባኤያት ባልተስፋፋበት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል የእግዚአብሔርን አለመኖር አምኖ የተቀበለ ትውልድ ስለነበር ከአለማመን ወደ ማመን የተሸጋገረበት ጊዜ በመሆኑ የመናፍቃን ወጀብና የምእመናን ጥያቄ ተደማመሮ ያንገላታው ሕዝብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣ ነበር።

በዓለም ደረጃም የመጽሔት እና የጋዜጣ ኅትመትና ሥርጭት የተስፋፋበት ጊዜ በመሆኑ የቤተ

ክርስቲያንን ትምህርተ ወንጌል፣ ሥርዓት፣ ዶግማና ትውፊት በኅትመት መገናኛ ብዙኃናት እንደ አንድ ማሠራጫ መንገድ በማሰብ ማኅበሩ በቀዳሚነት የሐመር መጽሔት ኅትመትን ጀመረ ያም ወቅት መሠረታዊ የሆነውን ነገረ ሃይማኖትንና ቤተ ክርስቲያንን ለማወቅና ለመረዳት ትምህርተ ወንጌልን ማስተማር፣ አገልግሎቱንና መንፈሳዊ ሕይወቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል የማድረግ ሥራ ባስፈለገበት ጊዜ የመጀመሪያው የሐመር ዕትምም በቤተ ክህነት ሊቃውንት ጉባኤ ታይቶ በመጽደቁ ለገበያ ዋለ፡፡

ቀደምት አገልጋዮችም እነ መምህር ብርሃኑ ጎበና፣ ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ ቀሲስ ኤፍሬም እሸቴ፣ ግርማ ወለድ ሩፋኤል እንዲሁም መልአከ ሰላም ቀሲስ ደጀኔ ሽፈራሁ የተካፈሉበት የመጽሔቱ ዝግጅት በሺዎች የሚቆጠሩ አንባብያንን በወንጌል ለማነጽ የቻለ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም ከትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በተጓዳኝ ተወዳጅ የሆኑ ዐምዶችን እንደ ‹እናስተዋቃችሁ፣ ዓምደ ወራዙት፣ መንገደኞቹ፣ እንደሁም ኪነ ጥበብ› ይዞ በመምጣቱ የበርካቶች አስተያየትና ጥያቄ ወደ ማኅበሩ ኅትመት ዝጅግት ክፍል ይጎርፍ ነበር፡፡

በተሐድሶና በመናፍቃን ቅሠጣ ይሠቃይ የነበረው የዚያን ዘመን ምእመናን በሃይማኖታቸው በእጅጉ ይፈተኑ ስለነበር ለነበሯቸው ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ በመሻት ወደ ዝግጅት ክፍሉ በአካል በመምጣትም ሆነ ስልክ በመደወል እንዲሁም ደብዳቤ በመጻፍ በቂ ትምህርት ያገኙ ነበር፡፡ ሐመር መጽሔት የወቅቱን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ እና በዐምዶቹ ውስጥ በማካተት ለአንባብያኑ ተደራሽ ያደርግም ነበር፡፡ አንድ ሰው ክርስቲያናዊ ሕይወቱን በምን መልኩ መምራት እንዳለበት፣ ማኅበራዊ ሕይወቱ መንፈሳዊነቱን ጠብቆ እንዴት ሊሄድ እንደሚችል ለምእመናን ለማስተማርና ለማሳወቅ መርዳት የሚችልበትን መንገድም ቀይሶ የተነሣ መጽሔት በመሆኑ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ መቆየቱም የሚታወስ ነው፡፡ ወቅቱን ጠብቆ በየሁለት ወሩ ይታተም የነበረው ሐመር መጽሔትም በዚህ ሂደት ዘመናትን ተሻግሮ በአሁኑ ወቅትም መጽሔቱ በየወሩ በመታተም ላይ ይገኛል፡፡

## ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ

በማኅበሩ የምሥረታ ታሪክ አንድ ሌላ የስብከተ ወንጌል ማስፋፋይ መንገድ ተዘረጋ፣ የ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የመጀመሪያው የስምዐ ጽድቅ ኅትመት ለምእመኑ መድረስ ቻለ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ እና ዙሪያዋ በሚያጋጥሙ ችግሮችና ፈተናዎች፣ መልካም ተግባራትና እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ልማት ለምእመኑ ለማሳወቅ እንደሚያስፈልግ በማመን በዘገባ መልክ፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች ተኮር የሆኑ ጽሑፎችና በማዘጋጀት እንዲሁም በአገልግሎታቸውና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አርአያ የሆኑ የቤተ ክርስቲያንና የሃይማኖት አባቶችን በእንግዳነት በማስተናገድ መረጃ መስጠት ላይ ያተኮረ ወርኃዊ ጋዜጣን የማሳተም ተግባሩም በቋሚነት ተያዘ፡፡

ከዐምዶቹ መካከልም ‹‹ዜና፣ መልእክተ ስምዐ ጽድቅ፣ ድብዳቤዎቻችሁ፣ ኅብረ ነገር፣ ክርስቲያናዊ ሕይወት፣ እርስዎስ ምን ይላሉ?፣ ሕይወትን የሚፈቅድስ ሰው ማን ነው?፣ የአብርሃም ቤት እንግዳ፣ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ›› የተሰኙት ዐምዶች ይገኙበት ነበር፡፡ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ በተለይም ስብከተ ወንጌልን ከማሠራጨት እንዲሁም አስተዳደራዊ ችግሮችን ከመፍታትና ክፍተቶችን ከመሙላት አንጻር ሰፊ አበርክቶ የነበረው ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜም የጋዜጣው ተፈላጊነት ሲጨምር በየሁለት ሳምንቱ እንዲታተም ተደረገ፡፡

በሃይማኖት ፍቅርና ጽናት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል በቁጭት ተነሣሽነት የነበረው የዚያን ጊዜው አገልጋይ የማኅበሩ ትልቅ ኃይል ነበር፡፡ የወቅቱን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ችግሮች በመቋቋም የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ አስተምረዋል፡፡ በቂ አገልጋይና መሣሪያዎች ባልነበሩበት እንዲሁም የገንዘብ አቅም እጥረት በነበረበት ጊዜ እንኳን የአንባብያንን ፍላጎት ላለማስተጓጎል አገልግሎቱ በከፍተኛ ጥረት ይከናወን ነበር፡፡ የኅትመት አገልግሎቱ አሁንም እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## ቅዱሳት መጻሕፍት

ቅዱሳት መጻሕፍት መንፈሳዊ ዕውቀትን ለማካበት ከሚረዱን ንዋያተ ቅዱሳት ቀዳሚዎቹ ናቸው ይህንን እውነታ በመረዳት ማኅበሩ በ፲፱፻፺ ዓ.ም መጨረሻዎቹ አካባቢ የቅዱሳት መጻሕፍት መሸጫ መደብር ከፍቶ ስብከተ ወንጌልን ከማስፋፋት ባሻገርም ከሚያገኘው ገቢ የማኅበሩን አገልግሎት እያገዘ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ዘመናት በልዩ ልዩ መምህራን የተዘጋጁትን ቅዱሳት መጻሕፍትም በተመጣጣኝ ዋጋ ለአንባብያን ያቀርባል፡፡

በተለይም ምእመናን ቅዱሳት መጻሕፍትን ገዝተው

ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ማኅበሩ በልማት ተቋማት አስተዳደር ሥር የንዋያተ ቅዱሳት መሸጫ መደብር በመክፈት ከቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጋር የማይጋጩ ጠቃሚና ማሳያ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶችን በስፋት እና በተሻለ ጥራት እያመረተ ያቀርባል፡፡ በዚህም ለምእመኑ ስብከተ ወንጌልን ከማሠራጨቱም ባሻገር ከገቢው በሚያገኘው ገቢ የማኅበሩን አገልግሎት እየደገፈ ይገኛል፡፡

ማኅበሩ ካሳተማቸው መጻሕፍት መካከልም የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወትና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የሚያጠናክሩ እንዲሁም በነገረ ሃይማኖት፣ እቅበተ እምነት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ገድላት፣ ድርሳናት፣ የሕፃናት መጻሕፍት፣ የግቢ ጉባኤያት መጻሕፍት፣ ሥነ ጽሑፍ እንዲሁም ቁጥራቸው ከ፻ (መቶ) በላይ የሚሆኑ ሌሎች መጻሕፍትን ለአንባብያኑ ማበርከቱንም መረጃው ያመለክታል፡፡

## መጽሔት ተልእኮ ዘማኅበረ ቅዱሳን

ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ አገልግለቱን ለማስተዋወቅ የብዙ ዓመት ምኞቱ ስለነበር በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም እንደ ድልድይ የተጠቀመባትን መጽሔት አሳተመ፡፡ ስያሜዋንም ‹‹መጽሔተ ተልእኮ ዘማኅበረ ቅዱሳን›› በማለት በማኅበሩ ጽሕፈት ቤት፣ በንዑሳን ማእከላት፣ በወረዳ ማእከላት እና ግቢ ጉባኤያት የተከናወኑ አገልግሎቶቹን የሚያስተዋውቁ ዓምዶችን አካቶ በዓመት ሁለት ጊዜ አሳትሞ ማሰራጨት ጀመረ፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ ግን አንድ ችግር ከፊት ለፊት ተጋረጠበት፡፡ ይሄውም መጽሔቱ በነጻ የሚሠራጭ እንደመሆኑ ለማኅበሩ ዋና ማእከላት፣ ለግቢ ጉባኤያት እንዲሁም ወረዳ ማእከላት፣ ለቤተ ክህነትና ለባለ ድርሻ አካላት፣ ለተለያዩ ተቋማት እና አካላትም ሆነ ለምእመኑ የሚደርሰው ከ፶፻ (አምስት ሺህ) ያልበለጠ ቅጂ በቂ አልነበረምና ነው፡፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የኅትመት ሚዲያው ማስታወቂያ ስለማይሠራለት እንዲሁም የማኅበሩ የገቢ ምንጭ አነስተኛ ስለ ነበር፡፡ አንባብያኑም የሚደርሳቸው ቅጂ በቂ እንዳልነበር በየጊዜው ይገልጹ ነበር፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ግን ማኅበሩ በመጽሔቱ የአንባብያንን አስተያየት ጥያቄዎች ለማካተት ይረዳ ዘንድ ‹‹ደብዳቤዎቻችሁ›› በሚል ዓምድ በመክፈት ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት አድርጓል፡፡ የመጽሔቱ አገልግሎት ተደራሽነት እየሰፋ ሲሄድም በሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ ሥር ሆኖ በዓመት ሦስት ጊዜ በየዐራት ወራት ልዩነት መታተምና መሠራጨቱን ቀጥሎ ነበር፡፡

በአሁኑ ጊዜ የተመረጡ ፻፷ (አንድ መቶ ሃያ) መዝሙራትን የትርጉም ሥራ በመሥራት በተለያዩ ከ፶ በላይ ቋንቋዎች የመዝሙር አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በክስታንኛ ቋንቋ ፳፬ መዝሙራት እና በሲዳምኛ ቋንቋ በተመሳሳይ ፳፬ መዝሙራት ተዘጋጅተው በዚህ ዓመት ለምእመናን መድረስ ችለዋል፡፡

## ወንጌልን በዝማሬ

### የመዝሙርና ኪነ ጥበባት አገልግሎት (መዝሙር በድምፅና ምስል)

ማኅበረ ቅዱሳን ከምሥረታው ጀምሮ የመዝሙርና ኪነ ጥበባት ክፍልን በማቋቋም በሰማያዊ የመላእክት ሥርዓት በተመሠረተ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ያሬዳዊ ዜማ የተለያዩ መዝሙራትን በተለያዩ ቋንቋዎች በልዩ ልዩ መንገዶች ለምእመናን ሲያደርስ ቆይቷል፡፡ በድምፅ እና በምስል ካሴቶች፣ በተለያዩ ሐዋርያዊ ጉዞዎች በዐውደ ምሕረትና ታላላቅ የዐደባባይ በዓላት በዘመኑ ቴክኖሎጅ በመታገዝ በዩቲዩብ በሬድዮ እና በቴሌቪዥን ጭምር መዝሙራቱን ለምእመናን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡ እስከአሁንም

በአማርኛ ዘጠኝ የመዝሙር ካሴቶች፤ አንድ የበገና ካሴት፣ ሰባት ቪሲዲ እንዲሁም አምስት የመዝሙር ጥራዞችን አጠቃሎ አንድ መጽሐፍ (አኮቴተ ያሬድ) አሳትሟል፣

በኦሮምኛ ዐራት የመዝሙር ካሴቶች(ሲዲ)፤አንድ የበገና መዝሙር ካሴት፣ ሁለት የመዝሙር ቪሲዲ እንዲሁም ሁለት የመዝሙር ጥራዞች፤ አንድ የበገና መዝሙራት ጥራዝ አሳትሟል፣

በትግርኛ ሦስት የድምጽ መዝሙር ካሴቶች፣አንድ የበገና ሲዲ፣ አንድ ቪሲዲ፣ እንዲሁም አንድ የመዝሙር ጥራዝ አሳትሟል፣ በጉራጌኛ፣ በወላይትኛ፣ በኪስታኒኛ እና በሲዳሚኛ አንዳንድ የመዝሙር ሲዲዎች አሳትሟል፡፡

## ሐዊረ ሕይወት እና በረከቱ

ማኅበረ ቅዱሳን ሐዊረ ሕይወትን የጀመረው አባላቱን ብቻ ያሳተፈ መንፈሳዊ ጉዞ በማዘጋጀት በ፳፻፩ ዓ.ም ነው፡፡ በዚያን ጊዜም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወረ በዓመት ሁለት ጊዜ ማለትም በስብከተ ጾምና በዐቢይ ጾም ወቅት ያዘጋጅ ነበር፡፡ የአባላት ኃላፊ የነበረው ዲያቆን ሙሉ ዓለም ካሣ ‹‹ሐዊርያዊው ጉዞ ሰፍቶና ከአባላት ውጪ ምእመናንን በሚያሳትፍ መልኩ ቢዘጋጅ›› የሚል ሐሳብ በማንሣቱ በሥራ አስፈጻሚ በጸደቀው ውሳኔ መሠረትና ስያሜውንም በመቀየር የ‹ሐዊረ ሕይወት› መንፈሳዊው ጉዞ ተስፋፍቶ ቀጠለ፡፡ ያን ጊዜም ጀምሮ በጉዞው አባላትን ጨምሮ ከሦስት ሺህ በላይ ምእመናንን የሚያካትትና ምክረ አበውን ታሳቢ ያደረገ መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡ የመጀመሪያው ሐዊረ ሕይወት የተካሄደው ደብረ ጽጌ ማርያም ሲሆን ፫፻፭ (ሦስት ሺህ አምስት) ሰው የተሳተፈበት ነበር፡፡

## ገዳማት እንዳይፈቱና አብነቱ ያለ አብነት እንዳይቀር ከመደገፍ አንፃር የተሠሩ ሥራዎች

ማኅበረ ቅዱሳን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲስፋፋና የአማንያኑ ቊጥር እንዲጨምር ለማድረግ ከሥር መሠረቱ በተለይም ሕፃናቱን በትምህርተ ሃይማኖትና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ኮትኩቶ ለማሳደግ የአብነተ ትምህርት ቤቶችን እያስፋፋ ይገኛል፡፡ የማኅበሩ የቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ከተዋቀረበት ዓመት ምሕረት ጀምሮ አብነት ትምህርት ቤቶች ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች የአበንት ቤቶችን ሲያፋፋ ነባሮቹን ደግሞ የማጠናከር ሥራ ሠርቷል፡፡ በዚህም የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ ገዳማትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በሁለንተናዊ መልኩ የሚጠናከሩበትን መንገድ ተመቻችቷል፡፡ ገዳማትም ራሳቸውን በኢኮኖሚና በልማት እንዲችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ እንደሆኑ ተደርገዋል፡፡

ይህም የአብነት ትምህርት ቤቶች መገንባትና መስፋፋት ከገዳማትና አብነት ትምህርት ቤቶች በሁለንተናዊ መልኩ ብቁ የሆኑና ዘመኑን የዋጁ አገልጋዮችን ማፍራት ችሏል፡፡ አገልግሎቱም በአንድ በኩል የምእመናንን ቁጥር ሲጨምር በሌላ መልኩ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚያጠናክሩ አገልጋዮችን አስገኝቷል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ማኅበሩ የገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ክብርና ህልውና ተጠብቆና ተጠናክሮ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በሁለንተናዊ መልኩ እድገት እንድታገኝ ማኅበረ ቅዱሳን የድርሻውን እየተወጣ ነው፡፡ የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በገንዘብ፣ በዕውቀቱና በጉልበቱ እንዲያገለግል አስፈላጊውን ሁሉ ማመቻቸት፣ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥናት የሚያደርጉ ሰዎችን በተለይ ወጣት ምሁራንን ማበረታታና በሚቻለው ሁሉ መርዳትም ከማኅበሩ ዐበይት ተግባራት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## አገልግሎቱ ያስገኛቸው ዋና ዋና ለውጦች

መረጃው እንደሚያመለክተው፤በጕአድራጊ ምእመናንና ማኅበራት ከተናጠልና ጊዜያዊ ድጋፍ ይልቅ የተቀናጀ ዘላቂ ልማት ላይ በማተኮራቸው ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሆኑባቸው ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች የሚከተሉትን ለውጦች ለማየት ተችሏል፡፡

በገዳማት የተፈጥሮ ሀብት ወደ ልማት ለመለወጥ ያላቸው የተነሣሽነትና ቁርጠኝነት መጨመር ለሌሎች አርአያ መሆን ነው፤ ለምሳሌ፡- በልበሊት ምዕራፈ ቅዱሳን ኢየሱስ ገዳም፣ ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም፣ አቃቂ አባ ሳሙኤል ገዳም በገዳማት መተዳደሪያ ማግኘት በመቻሉ መናንያን በገዳማቸው ጸንተው የመኖር ፍላጎታቸው ጨምሯል፡፡ ለምሳሌ፡- ከሣቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ገዳም፣ ጉንዳጉንዶ ቅድስት ማርያም ገዳም፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም በውኃ እጥረት ይቸገሩ የነበሩት ገዳማት ችግር በመቅረፍ የመናንያን ቁጥር መጨመር፣ አቡነ ቶማስ ዘሃይዳ ገዳም፣ ምድረ ከብድ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም፣ ደብረ ሃሌ ሉያ አቡነ ሳሙኤል ገዳም ተማሪ በማጣት ተስፋ ይቆርጡ የነበሩ መምህራን ተማሪ በማግኘት ትምህርታቸው ዋጋ የተሰጠው መሆኑን በመረዳት ተስፋቸው መለምለሙ፤ ምሳሌ፡- ዋሸራ ደብረ ምዕራፍ፣ ሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ሰለልኩላ ቅዱስ ሚካኤል የአብነት ትምህርት ቤቶች የተሻለና ምቹ የመማሪያ ሁኔታ በመፈጠሩ ተማሪዎች በአግባቡ ትምህርታቸውን መከታተል፤ ችለዋል፡፡

ቅድስት ቤተልሔም የድጓ ትምህርት ቤት፣ ሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ መጽሐፍት ትምህርት ቤት በአብነት ትምህርት ቤቶች በሚደረገው ድጋፍም የካህናት እጥረት ያለባቸው ጠረፋማ አካባቢዎች አገልጋይ ማግኘት ከቻሉት መካከል ናቸው፡፡ የአብነት መምህራንና ተማሪዎች ከአብነት ትምህርቱ በተጨማሪ በስብከተ ወንጌልና በተጨማሪ ሥልጠናዎች ለመሳተፍ ያላቸው ፍላጎት ማደግና ለተለያዩ ክህሎት ተሳታፊ መሆን በዚህም በአገልግሎት የሚተጉ ካህናት ማግኘት ዋና ዋናዎቹ የተመዘገቡ ለውጦች ናቸው፡፡

## የማኅበሩ አሻራዎች በአብያተ ክርስቲያናት ሕንጻ ግንባታ የፕሮጀክት ሥራዎች

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባልን ሁሉ መሰብሰቢያችን በመሆኗ ቅድስት ቤታችንን ልናንጽና ልንጠብቅ እንደሚገባ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ሲል አስተምሮናል ‹‹ቤቴንም ሥሩ፡፡›› የእግዚአብሔር ቤት ቅድስናው ተጠብቆና ሥርዓቱ ሳይፋለስ ለሕዝበ ክርስቲያኑ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ዋጅቶ የመሠረታት ቅድስት ቤቱን በአምሳለ ግብሩ ተምሳሌት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን እናንጻለን የሚል ሲሆን፡፡ የባለፉትን ፲፪ ዓመታት (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሦስት ሺህ) ብር ግምት የሚያወጡ ፳፯፻፹፪ ለሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናትን የጠበቁ የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ዲዛይኖች ተሠርተዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከአብያተ ክርስቲያንን ኦርቶዶክሳውያን የሚጠየቁ በርካታ የፕሮጀክት ቀረጻ ጥያቄዎችንም ተስተናግደዋል፡፡

## በማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፍ

ማኅበራዊ አገልግሎት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንዱ ተልእኮ ነው፤ ይህ አገልግሎት ማኅበራዊ ወንጌል ተብሎም ይጠራል ይላል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ ዘርፍ ሰፊ አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯልም፡፡ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በገንዘብና በዓይነት ድጋፍ በማሰባሰብ ድጋፎችም ለተሰበሰቡለት አገልግሎት እንዲውሉም አድርጓል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ቀውሶች የተነሣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ለገጠማቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች የአስቸኳይ ድጋፍና የመልሶ ማቋቋም ድጋፎችን አድርጓል። በተለይ ከጥቅምት ፲፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የመልሶ ማቋቋምና አስቸኳይ ድጋፍ ዐቢይ ኮሚቴ በማቋቋም፣ በተከታታይ በደረሱ ሃይማኖታዊ ጥቃቶችና ማኅበራዊ ቀውሶች ለተጎዱ አካላት ድጋፎችን ማድረጉ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ በተለያዩ ክፍለ ሀገራት ለደረሰው የማኅበራዊ ሕይወት ቀውስን በመረዳት ለችግሩ መፍትሔ ይሆን ዘንድ ለተጎጂዎቹ ርዳታ ከሰጠባቸው አካባቢዎች ውስጥ ለአብነት ያህል የአጋርፋ ወረዳ አምቤንቱ ለ፲፻፪፻፶፫ (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ኀምሳ ሦስት) ተጎጂዎች እና አዳባ ለአራት መቶ ዐርባ ተጎጂዎች የምግብና የጽዳት ዕቃዎች ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፤ ደብረ ምጥማቅ ሰአተ ምሕረት ቅድስት ማርያምና ክርስቶስ ሳምራ ከዕውቀት ብርሃን ሰንበት ትምህርት ቤት ጋር በመሆን ቦታው ላይ በመገኘት በጋራ የተደረገውን ርዳታ መጥቀስ ይቻላል፡፡

የተጎዱትንም መልሶ ለማቋቋም ማኅበሩ የእነዚህን የአልባሳትና የገንዝብ እንዲሁም የሕክምና ርዳት ቡልቡላ ለ፳ (ሃያ) አባወራ፣ በኮፈሌና ቆሬ ወረዳ፣ በአዳባ ወረዳ ለ፻፳፰ (መቶ ሃያ ስምንት) አባወራዎች፣ በአጋርፋ ወረዳ ኦዳ ነገሌ ቀበሌ ለ፳፱ (ሃያ ዘጠኝ) ተጎጂዎች፣ በኮፈሌ ወረዳ ለሚገኙ ወጣቶች፣ በዶዶላ ወረዳ ፮፻፸፭ (ስድስት መቶ ሰባ አምስት) አባወራዎች እና ፳፮ (ሃያ ስድስት) ተጎጂዎች፣ ከሻሸመኔና ከአሰበ ተፈሪ ተፈናቅለው አዲስ አበባ ለሚገኙ ሦስት እማወራዎች፣ ለዝዋይ ለዱግዳ፣ ለሔረሮ፣ ለሻሸመኔ ለአዋሾ እንዲሁም መጋቢት ፲-፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም አጣየና አካባቢው በነበረው ችግር ጉዳት ለደረሰባቸው ፲፮ (ዐሥራ ስድስት) ተጎጂዎች፣በትግራይ ክልል ለሚገኙ ችግር ለገጠማቸው ሕፃናት፣ በደሴና በአካባቢው ተፈናቅለው የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ በደባርቅና ጭና፣ ከሰሜን፣ ደቡብ ወሎና ሰሜን ሸዋን የተለያዩ አካባቢዎች ተፈናቅለው ደብረ ብርሃን ከተማ ለሚገኙ ተፈናቃዮች በማኅበሩ ድጋፍ ተደርጐላቸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በኮፈሌ ወረዳ የሚገኙ ወጣቶች እንዲደራጁና መንፈሳዊ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ የመጽሐፍትና የሻይ ክበብ እንዲኖራቸው የቁሳቁስ፣ በወሊሶ አካባቢ ጉዳት ለደረሰባቸዉ ፷፭ (ስድሳ አምስት) ቤቶች በሰኣሊተ ምሕረት ሰንበት ትምህርት ቤት ወሊሶ ማእከል ክትትል የጥገና ሥራ ተሠርቶ ተጎጂዎችን ረድቷል፡፡ በአጠቃላይ ማኅበሩ በጐ አድራጊ አካላትን በማስተባበር በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ለዚህ አስቸኳይ ማኅበራዊ ድጋፍ ከ፳፻፻ (ሃያ ሚሊዮን) ብር በላይ ወጭ አድርጓል፡፡

## በዚህ ዓይነት ማኅበረ ቅዱሳን ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተክርስቲያኒቷ መዋቅር ዕውቅና አግኝቶ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በጠቅላይ ቤተክህነት በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር መደራጀቱ ይፋ ሆነ። በዚህ ወቅት ለማኅበሩ ምሥረታ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊዎች ትልቅ አስተዋጽኦ ነበራቸው።

በቀጣይም ማኅበሩ በልማቱም ሆነ በስብከተ ወንጌል አገልግሎቱ በርከታ ሥራዎችን ለማከናወን መርሐ ግብር አዘጋጅቷል።

### የማኅበሩ ጥናትና ምርምር መዳረሻ

ማኅበረ ቅዱሳን በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት ጥናትና ምርምር

ማእከል›› በመክፈት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተዋወቅ እና ከሚደርስባቸው ልዩ ልዩ ጉዳዮች አደጋዎች ተጠብቀው ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ ያቋቋመው የአገልግሎት ክፍል ለዛሬው የጥናትና ምርምር ማእከል መመሥረት ምክንያት ነው። ይህ ክፍል በተሻለ አደረጃጀትና የሰው ኃይል ተጠናክሮ ከኅዳር ወር ፳፻፩ ዓ.ም ጀምሮ ‹‹የማኅበረ ቅዱሳን ጥናትና ምርምር ማእከል›› በሚል ስያሜ አገልግሎት መስጠት ጀምሮአል።

የጥናትና ምርምር ማእከል በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ ጥናትና ምርምር እንዲለመድ ምሁራንም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት እንዲያዘጋጁ ለማደፋፈር ውጤቶቹንም ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አካላት እና ምእመናን በተለያዩ መንገዶች ለማድረስ እና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የሐሳብ፣ የሞያና የገንዘብ ድጋፍ ለማበርከት የተቋቋመ ነው። ማእከሉ በርካታ የውይይት መድረኮችን፣ ዓመታዊ የጥናት ጉባኤ እንዲሁም የምርምር መጽሔት አዘጋጅቷል።

እስካሁንም፤ ከ፳፻፻ (ሁለት መቶ ሺህ) በላይ ምሁራንና ተመራማሪዎች የተሳተፉባቸው ከ፻ (መቶ) በላይ ጥናቶችና የምርምር ግኝቶች በመድረክ ቀርበዋል። ሦስት ዓለም ዓለማቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን የጥናት ጉባኤያት ተካሂደዋል። (ሁለት በአውሮፓና አንድ በአሜሪካ)

### ግቢ ጉባኤያት

ማኅበራችን በግቢ ጉባኤ ሰፊ አገልግሎት እንደሚሰጥ የሚታወቅ ሲሆን ማእከላት የከፍተኛ ተቋምትን በማቋቋም፣ የግቢ ጉባኤያት ሥራ አስፈጻሚዎችን በማዋቀር እንዲሁም መምህራንን በመመደብ በግቢ ጉባኤ ቆይታቸው ተማሪዎች መማር ያለባቸው መንፈሳዊ ትምህርቶች እንዲማሩ አድርጓል። በግቢ ጉባኤያት አገልግሎት ማስተባበሪያ አማካኝነት በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥ ፬፻፵፩ (አራት መቶ ዐርባ አንድ)፣ በውጭ ሀገራት (በተለይ በሩቅ ምሥራቅ፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓና በካናዳ) ፱ (ዘጠኝ)፣ በድምሩ ፬፻፶ (አራት መቶ ሃምሳ) ግቢ ጉባኤያትን መመሥረት ተችሏል። በእነዚህ ተቋማት ውስጥም በዓመት በአማካይ እስከ ፫፻፶፻ (ሦስት መቶ ኀምሳ ሺህ) ተማሪዎችን በአባልነት አቅፎ ተከታታይ የነገ ሃይማኖት ትምህርቶችን ያስተምራል።

(ይህ ቁጥር ከዓለም ትናንሽ የሕዝብ ብዛት ያላቸው

ዐሥር ሀገራት የሕዝብ ቁጥር ድምር ጋር ተቀራራቢ ስለሆነ በቀላሉ የሚታይ አይደለም) ግቢ ጉባኤያቱ መንፈሳዊ ትምህርቶቻቸውን ተከታትለው መመረቅ

ከጀመሩበት ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ጀምሮም እስከ ፳፻፲፩ ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ከሰባት መቶ ሺህ በላይ ተማሪዎችን በአበው ቡራኬ ማስመረቁም መረጃው አመልክቷል፡፡ ሁሉም ግቢ ጉባኤያት በተቀመጠው የግቢ ጉባኤያት መዋቅር መሠረት አገልግሎታቸውን እያስኬዱ ይገኛሉ፡፡

## ግቢ ጉባኤያት ለሀገር እና ለቤተ ክርስቲያን ምን አበረከቱ?

### ግቢ ጉባኤ ለቤተ ክርስቲያን

የቤተ ክርስቲያን ዋና እና ተቀዳሚ ተግባሯ ሁሉም የሰው ልጅ ድኅነት እንዲያገኝ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ምሥጢራትን በመፈጸም ታከናውናለች፡፡ የሰው ልጅ የመዳን ዕውቀትን ዐውቆና ምሥጢራትን ፈጽሞ በሁለንተና ሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር አንድ እንዲሆን የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የመዳንን ዕውቀት የሚያስተምሩ መምህራንን መድቦ የሕይወትን ቃል ይመግባል፡፡ ግቢ ጉባኤ ይህንን የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ በብዙ መንገድ ያከናውናል፡፡

፩ኛ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርትን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓቷን፣ ሕጓን፣ ዶግማዋና ቀኖናዋን በደንብ እንዲያውቁ አድርጓል፡፡

፪ኛ በግቢ ጉባኤ ተምሮ ተመርቆ የወጣ ተማሪ በሥራው ዓለም ተቀጥሮ ሲኖር የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ሕግ የሚጠብቅ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ዐሥራት ማውጣት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው፡፡ በግቢ ጉባኤ ተምሮ የወጣ የመንግሥት ሠራተኛ ከዐሥር አንድ ለቤተ ክርስቲያን እየሰጠ ቅዳሴው እንዲቀደስና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይቋረጥ የተቻለውን ያህል ያደርጋል፡፡

፫ኛ ግቢ ጉባኤ የአብነት መምህራንን ቀጥሮ ተማሪዎች ከመደበኛው የዩንቨርሲቲ ትምህርታቸው ጎን ለጎን የአብነት ትምህርት እና የግእዝ ትምህርት እንዲማሩ አድርጎ ብዙዎችን ለክህነት እንዲበቁ አድርጓል፡፡ ይህም አሁን አሁን የሚታየውንና በሀገሪቱ አብያተ ክርስቲያናት ያለውን የካህናት እጥረት ለመቅረፍ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው፡፡ ብዙዎች ተምረው ዲያቆናትና ቀሳውስት ሆነው ወጥተዋል፡፡ አሁን በተመደቡበት የሥራ ቦታም የንስሓ አባት ሆነው ምእመናንን በማስተማርና ያላመኑትን በማሳመን ትልቅ አስተዋጽኦ እንዲያደረጉ ያስችላል፡፡

፬ኛ በግቢ ጉባኤ ተምሮ የወጣ ተማሪ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ወጪ የምታወጣባቸውን የተለያዩ ፕሮጀክቶች በሙያው በነጻ እያገለገለ ቤተ ክርስቲያንን ብዙ ወጪ ከማውጣት ታድጓታል፡፡ ይህም የግቢ ጉባኤ መቋቋም ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳል፡፡

### ግቢ ጉባኤ ለሀገር

መረጃው ግቢ ጉባኤ ለቤተ ክርስቲያን ካለው ጠቀሜታ በተጨማሪ ለሀገርም ያለውን ጠቀሜታ እንደሚከተለው በዝርዝር ያሳያል፡፡

፩ኛ ግቢ ጉባኤ በሥነ ምግባር የታነፀ፣ ሙስናን የሚጠየፍ፣ ታማኝ፣ የሀገሩን ምሥጢር የሚጠብቅ፣ ዘረኝነትን የሚጠላ፣ ሁሉንም ሰው እንደራሱ የሚወድ ሰውን ያፈራል፡፡ በግቢ ጉባኤ የሚሰጠው ትምህርት ሰውን ሁሉ ስለመውደድ ነው፡፡ ስለሆነም ከግቢ ጉባኤ ተመርቆ የመጣ ትውልድ ሙስንናን የሚጠየፍው ሰው ስላየውና ስላላየው ሳይሆን ‹‹በሁሉ ቦታ ያለ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር ያየኛል›› ብሎ ክፉ ከመሥራት የሚቆጠብ ትውልድ ይሆናል፡፡

፪ኛ በግቢ ጉባኤ ያለፈ ተማሪ ሀገሩን የሚወድ ነው የሚለው መረጃው፤ ሀገሩን የሚወድ ማለት በሀገሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን እንደራሱ የሚወድ ማለት ነው፡፡

፫ኛ መረጃው በግቢ ጉባኤ የተማረ ትውልድ ሁሉን በእኩል የሚያይ እና አድሎ የማያደርግ ትውልድ ሆኖ ይወጣል፡፡

፬ኛ ደረጃም በግቢ ጉባኤ ያለፈ ትውልድ ለሀገር ተቆርቋሪ ወይም ሀገር ወዳድ እንዲሁም ታታሪ ሠራተኛ እንዲሆን ተደርጐ ነው የሚቀረጸው በግቢ ጉባኤ ተምረውና ተመርቀው የወጡ በብዙ መቶ ሺህዎች የሚገመቱ ዜጎች ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሠሩትና እየሠሩ ያሉት ውለታ አሁን ላይ ሕያው ምስክር ነው፡፡

## ማኅበረ ቅዱሳን በግቢ ጉባኤያት ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት

### በመንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፍ

ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርተ ወንጌል በሀገሪቱ ውስጥና ውጭ ባሉ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች አቅም በፈቀደ መጠን ቃለ እግዚአብሔርና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ መንገድ ሲያስተምር ቆይቷል፡፡ የዐውደ ምሕረት ስብከቶችና ትምህርቶች ሥልጠናዎች

እና ዐውደ ርእያት እንዲሁም የኅትመት ውጤቶች ዋናዎቹ የማስተማሪያ መንገዶች ነበሩ፡፡

በሁሉም ግቢ ጉባኤያት ወጥ የሆነ እና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለማስተማር ይቻል ዘንድ ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽ ፬፻፸፩ (በአራት መቶ ሰባ አንድ) የሀገር ውስጥ ግቢ ጉባኤያት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ፳ (ሃያ) መጻሕፍት ታትመው በግቢ ጉባኤያት አገልገሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ የሚያመለክተው መረጃው፡፡

አዲስ አበባ የሚገኘው የማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል ጽሕፈት ቤት ሕንጻ ግንባታ በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ የግቢ ጉባኤያት ድርሻ ከፍተኛ እንደነበረም አመልክቷል፡፡ (ጉባኤ ቃና ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጋዜጣ፤ ፫ኛ ዓመት፤ ቁጥር ፬፤ ሚያዝያ ፳፻፪ ዓ.ም)

### የግቢ ጉባኤያት ፍሬዎች ለቤተ ክርስቲያን

ማኅበረ ቅዱሳን ላላፉት ፳፱ (ሃያ ዘጠኝ ዓመታት) ዓመታት በግቢ ጉባኤያት ላይ ባደረገው አስተዋጽኦ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚጠቅም ተውልድን በድርሻው እያፈራ ይገኛል፡፡ በግቢ ጉባኤ የሚገኙ ተማሪዎችም የትምህርት ቆይታቸውን በከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ለሌሎችም አርአያነታቸውን በማስመስከር ላይ ይገኛሉ፡፡ በውጤታማነታቸውም በየዓመቱ የዋንጫና የሜዳልያ ተሸላሚዎችን መመልከት የተለመደ እየሆነ መጥቷል፡፡ የሃይማኖት ትምህርቱ ከዩኒቨርሲቲው ትምህርት ጋር ይጋጫል እያሉ የሚያዘናጉትን በውጤታቸው በማሳፈር ውጤታማነታቸውን እያስመሰከሩ ናቸው፡፡

ለሜዳልያ ዋንጫ ተሸላሚነት የበቁት ተማሪዎቹ ቊጥራቸው ከፍተኛ እየሆነ ከመመጣቱ ጋር ተያይዞ ለውጤታማነታቸው መሳካት ምሥጢሩ ‹‹በግቢ ጉባኤ መታነፃቸው›› እንደሆነም ራሳቸው በአንደበታቸው ይመሰክራሉ፡፡ እንደ ማኅበርም ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት የመጡበትን ዓላማ በአግባቡ በማስረዳትና የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች እንዴት መወጣት እንዳለባቸው እንዲሁም ለትምህርታቸው ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት ግቢ ውስጥ እንዴት መቆየትና በምን መልኩ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ በቂ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፡፡ የጊዜ አጠቃቀም ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በቂ ዕውቀትም እንዲጨብጡ ይደረጋል፡፡ ሁለቱንም እንዴት አጣጥመው ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ በበቂ ሁኔታ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት የተነገራቸውን በአግባቡ በመተግበር ከፍተኛ ነጥብ አምጥተው በዋንጫና በሜዳልያ ይመረቃሉ፡፡

ባለማዕረግ ተመራቂዎቹም ‹‹ማኅበረ ቅዱሳን ለውጤታማነታችን ባለውለታችን ነው›› በማለት ዋንጫቸውንና ሜዳልያቸውን አምጥተው ለማስተዋሻነት ለዋናው ማእከል ጽሕፈት ቤትና ለማእከላት ይሰጣሉ፡፡ ማኅበሩም ዋንጫቸውንና ሜዳልያቸውን በክብር ተቀብሎ በአግባቡ ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ለሰው በሚታይ ሥፍራ በአንድ ላይ አሰባስቦ በክብር ያስቀምጣል፡፡

በግቢ ጉባኤያት አገልግሎት በብዙ መልኩ አርአያ የሚሆኑ ዜጎችን መፍጠር ተችሏል፡፡ በሁለት ወገን የተሳሉ ሰዎች ልበ ብርሃን በመሆናቸው አስተዋይነት ገንዘባቸው ነው፡፡ ‹‹አስተዋይነት ያልታከለበት ዕውቀት ለውድቀት›› እንደሚባለው ከመውደቅ በፊት አስተዋይነትን ገንዘብ ልናደርግ ይገባል ሲል ይመክራል፡፡ ሀገራዊ ሀብት የሆነውን የግእዝ ቋንቋን ዳግም ለማንሣት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ብሔራዊ ስሜትን በመፍጠር ላይ ግቢ ጉባኤያት ድርሻቸው የላቀ ነው፡፡ ለቤተ ክርስቲያን የሚቆረቆሩ እና ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚጋደሉ የቁርጥ ቀን ልጆችን ከግቢ ጉባኤያት ማፍራት ችለናል፡፡ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን በማስከፈት መምህራን እና ሰባክያነ ወንጌል በመቅጠር የግቢ ጉባኤያት ተመራቂዎች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡

የግቢ ጉባኤው አባላት የቦታ ርቀት ሳይገድባቸው በየደብሩ እየተገኙ ቃለ እግዚአብሔር ከመማር፣ የአደባባይ በዓላትን ከማድመቅና ከማሳመር ባለፈ በልማት ሥራም በመሳተፍ ጉልህ አስተዋጽኦ እያደረጉ ናቸው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ቅድስት ቤተክርስቲያን በሰጠችው ተልኮ ላለፉት ፴ ዓመታት በርካታ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ያከናወነ ሲሆን በቀጣይም ዘመኑን የዋጁ አገልግሎቶችን ለመፈጸም የአምስትና የአሥር ዓመታት እቅዶችን አውጥቶ ለማገልገል ተዘጋጅቷል፡፡